# በሴቶች ድርጅት ላይ የተሸረበ ሴራ

ጫልቱ

ሀገር አጥፊው ወያኔ ኢትዮጵያን ለማውድም ከተነሳ ጀምሮ ህገወጥ ስልጣኑን ለመጠበቅ በቅድሚያ የሕዝብን ድርጅቶችና ተቋሞች ማፍረስን ዓላማዬና ግቤ ብሎ የተያያዘው ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ደግሞ የወያኔ ብቻ ጠባይ ሳይሆን የማንም ፍፁም አምባገናናዊ አገዛዝ መለያ ነው፡፡ መለስ ዜናዊ በተለይ የሶቭየት ህብረትን ሚች አምባገነን ጆሴፍ ስታሊንና የእሱ ተከታይ የነበረውን የአልባኒያውን ኤንቨር ሆጃን አዳናቂና አምላኪ ነበርና በወያኔ ድርጅትም ስር ሆነ ለስልጣን ሲበቃ የሕዝብ ተቋሞችን መቆጣጠር ወይም ማፍረስ ዋናው ተልዕኮ ሆኗል፡፡

በዚህም መሰረት እነ ኢሕአፓንና ሌሎች ድርጅቶችንም ህገወጥ ብሎ ለማገድ ጊዜ አልወሰደበትም፡፡ ቢተባበሩትም ሊቀናቀኑኝ ይችላሉ ያላቸውንም ድርጅቶች ሳይ ውል ሳይድር አባሯል፤አሳዷል፡፡ በድርጅቶች ምትክ ተለጣፊ መቀፍቀፍም ስላስፈለገው ከፎረም 84 አስከ “ዴድ” ዎችን እንደ ጥንቸል ወልዷል፡፡ በተወሰኑ ልጆቹም ላይ አመለኛ ድመት ሆኖ እንደበላቸውም ታይቷል፡፡ በማያያዝም የሰራተኞችን ማህበር አፍርሶ በተለጣፊ ተካ፡፡ የተማሪዎችና ልዩ ልዩ ማህበራትንም አፈረሰ ፡፡ በነፃ ጋዜጠኞች ላይም ተነሳ፡፡ በሀገር ቤትና በባዕድም በሀይማኖት ተቋሞች ላይ ከፋፋይ በትሩን ሰነዘረ ፡፡ ተቃዋሚ ድርጅቶች ላይ አንጃ ፈጠረ ወይም እንዲከሰት አበረታታ፡፡ በባዕድ ሀገር ያሉ ዜጎች በብዛት በፀረ ወያኔነት ስለተሰለፉም በተለይ በእነሱ ተቋሞች ላይ የክፍፍል ጦሩን ሰበቀ፤ ወረወረ፤ በጎጥ፤ በሀይማኖች ወዘተ ከፋፈለ ፡፡ የሕዝብ አለኝታ የተባሉ ድርጅቶችም በዚሁ በያዝነው አዲስ ምዕተ ዓመት የአንጃን ተወሳክ ሊሸከሙ የግድ ሆኖባቸው ሲታገሉም እያየን ነው፡፡

በአሁኑ ጊዜ ይህ ወያኔያዊ የአንጃ ጥቃት እየተጠነሰሰ ያለው በሴቶች ድርጅት ላይ ነው፡፡ ከተመሰረተ አንድ ዓመት ያለፈውን ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ሴቶች ድርጅ ት ፖለቲካ አቅዋምና ዝንባሌ ባሻገር ሴቶች በፆታቸው ተሰባስበው ለመብታቸው እንዲታገሉ በአጭር ጊዜ ከፍተኛ አስተዋፅዖን እያደረገ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ዓኢሴድ አቅዋሙ ፀረ ጭቆና በመሆኑ ለወያኔ የሚጎረብጥ ሀይል ሆኖ መታየቱ አልቀረም፡፡ በመሆኑም ከተመሰረተ ጀምሮ በወያኔ ሴረ ተሸርቦበታል፤ ጥቃቶች ተሞክረውበታል፡፡ የፖለቲካ አንጃዎች በጣውንቶቻቸው ላይ እያሰራጩት ያለው ዘለፋና ክስም በዓኢሴድ ላይም ተወርውሯል፡፡ ለምን በስራችን አልሆነም ያሉ ክፍ ሎች ዓኢሴድን በተወሰነ ፖለቲካ ድርጅት ተከታይነትም ሊከሱ ሞክረዋል፡፡ መስራ ቾቹ ተስፋ ይቆርጡ ዘንድም ፈተናዎች ና ጋሬጣዎች ተጥለውባቸዋል፡፡ ዓኢሴድ እየሰፋ፤ ራዲዮኑም ሰፊ ተደማጭነትን እያገኘ፤ ሴቶች ከየቦታው በዙሪያው ሊደራጁ ፍቃደኛነትን እያሳዩ ሲመጡም አቅል የሚያሳጣ መጥፎ ቅናት የያዛቸው ክፍሎችና የለመደባቸው ከፋፋዮች በድርጅቱ ላይ ዘመቻቸውን አጧጡፉ፡፡ ይህ አፍራሽ ሴራቸው እየተባባሰ መጥቶ በአሁኑ ጊዜ ቢያንስ ሁለት የአንጃ ስብስቦች “የራሳችን” በሚል “የሴቶች ድርጅት” ሊመሰርቱ በመዘጋጀት ላይ መሆናቸው ተደርሶበታል፡፡ ያው የተንኮሉ ነፍስ አባት ወያኔ ነውናም የዓኢሴድንም ስም በለመደ አንጃዊ ቅሚያ (ወያኔ የቅንጅትን መልክት፤ሌሎችም የኢሕአፓን ስም አልሰረቁም?) የእኛ ነው ሊሉም እየቃጡ ነው ተብሏል፡፡ ይህ ርኩስ ሴራ ከዚህ በፊት

በቅንጅትም በኢሕአፓም ላይ ከተቃጣው አንጃዊ ሴራ በተለየ የረባ ውጤትን የሚ ያገኝ ባይሆንም በቀና መንፈስ የተጀመረውን የዓኢሴድ እንቅስቃሴ ለማደናቀፍና መደናገርንም ለመፍጠር የታቀደ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡

ነጋ ጠባ በሕዝብ ስም ቢምሉ ሆነ ለደሞክራሲና ለለውጥ ቆመናል ብለው ቢመፃደ ቁና እንባ ቢረጩም የሕዝብ ድርጅቶችንና ማህበራትን እየከፈሉ አንጃ ፈጥረው ለወያኔ የሚጠቅሙ ሁሉ ጎራቸው ከሕዝብ አይደለም፡፡ ቤተክርስቲያናትን የከፋፈሉ፣ ህዝብን በብሄረሰብና በሀይማኖት የለያዩ፣ ማህበራትና ተቋማትን በማፍረ ስ ከወያኔ የተባባሩ ሁሉና የቆሻሻ ቆሻሻ ደግሞ አንጃን የፈጠሩ፣ ብተናን የሞከሩ ሕዝብ ይቅር የሚላቸው አይሆኑም፡፡ ሴቶች ለመብታቸውና ለሀገራቸው ይታገሉ ዘንድ ብዙ ጥረት ተካሂዶ ዛሬ በዓኢሴድ መኖር የተስፋ ጭላንጭል ሲታይ ይህንኑ ለማዳፈንና ለማጨለም እያሴሩ ያሉትን አንጃዎችና ወያኔዎች በጥብቅ እያወገዝን ና ነቅተንም እየታገልን ለዓኢሴድ መጠናከር የበኩላችንን አስተዋፅዖ እናድርግ፡፡

አንጃኝነት የተወገዘ ይሁን!!
ፀረ ዓኢሴድ ሴራዎች ይከሽፋሉ!!